# ጎያሉ ሽብርተኛ



t.me/OLDBOOKSPDF

ደራሲ

ሌ.ደብልዩ.ሚኬል

THE LUXUS

# ኃያሉ ሽብርተኛ

ያሬድ ብርሃኑ ሣህሌ

ወደ'ማርኛ እንደመለሰው

t.me/OLDBOOKSPDF

## የያሬድ ብርሃኑ ሌሎች ስራዎች

- ፍቅር-ምገደኛው
- ማለዳ፣ ቀትርና ምሽት
- የጉብሊቷ ምስጢር
- ህልምሽን ንገሪኝ
- ህያው ገጹ-በረከት



የተርጓሚው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው።።

© ያሬድ ብርሃኑ ሣህሌ
ፖ.ሳ.ቁ 15872
የመጀመሪያ ዕትም - ፲፱፻፺ ጥቅምት

## ለታደሰ ሥዩም
## እና
## ለሰናይት በላቸው

ለዚያን ህዳር 8/1983 ዓ.ም. ለዋለው 'ጥቁር ቅዳሜ' የጥቁር አንበሳ ሆስፒታል የጭንቀት ሌሊት ይህች መጽሐፍ መታሰቢያ ትሁናችሁ:: በዚያን የጽልመት ለይል የመጨረሻ የስንብት ምጡን በተጋራችሁት ታናሽ ወንድሜ ዮሴፍ ስም ከነቤተሰባችሁ በምድር በረከቱን እንዲሰጣችሁ ፤ በሰማይ ኦ... እርስቱን እንዲያወርሳችሁ የዘወትር ምኞቴና ፀሎቴ ነው ::

**የሽፋን ምስል**

ሽብርተኛው በጭምብል

- ሽብርተኛ አዳኝ የአሜሪካን እና የእስራኤል ልዩ ኮማንዶ
- ከማል ናሲር (የፍልስጤሙ አርበኛ)

* ከታይምስ መጽሔት የተወሰደ



t.me/OLDBOOKSPDF

የሊቢያው ኮሎ... ... የአ... ... ... ... መብት
ክፉኛ ያሰጋቸዋል።
የታወቁ ምርጥ የእስራኤል ኮማንዶዎች የአሜሪካ ልዩ ኃይልና የሩሲያ ተወንጫፊ ብርጌድ በ21ኛው ክፍለ ዘመን የረቀቀ መሳሪያ እየታጠቁ አደኛ መዋጋ ያቃተቸው ኃያል ሽብርተኛ ማነው?
ሽብርተኞችን የደፈጣ ተዋጊዎችንና የግዳጅ ቡድኖችን በማሰልጠን በታላላቅ የዓለም መንግስታት ዘንድ የሚከበሩትን የሚፈሩትን አቡ ሀሰን ናስር ይህን ኃያል ሽብርተኛ ከምንም ዋጋ መትረፍ የማያስችለው ልዩ ሥልጠና ሰጥተውታል እንደ ብቸኛው ወንዱ ልጃቸው ከሚያዩ ናስር ጋር ከልብ ይወዱታል ከዚህም የተነሳ ከልጃቸው ጋር አብረው እንዲሰሩም በሃምብ ከፈራረሰው ተፈሪና የበረሃ ... ያሰለጥኑታል።

ዋጋ 20.00 ብር